የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ - ሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 48
ADDIS ABABA-22nd July, 2005

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......................................ገጽ ፫ሺ፩፻፶፯

## CONTENTS

*Council of ministers Regulation No. 119/2005*
"Construction Works & Coffee Technology Development Enterprise Establishment Regulation "............Page 3157

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም. "የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካልን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ ደንብ "የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>መቋቋም</u>
፩. የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ/የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
፪. "ድርጅቱ" በመንግሥት የልማት ድርጅቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 119/2005 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF CONSTRUCTION WORKS & COFFEE TECHNOLOGY DEVELOPMENT ENTERPRISE*

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and duties of the executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*
This Regulation may be cited as the "Construction Works and Coffee Technology Development Enterprise Establishment Regulation No. 119/2005".

2. *Establishment*
   1. It is hereby established the Construction Works and Coffee Technology Development Enterprise (hereinafter the "Enterprise") as a Public Enterprise.
   2. The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

የአንዱ ዋጋ 2·30
Unite Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Ngarit Gazeta P.O.Box 80001

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>
በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት
የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይኖናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. <u>ዓላማ</u>
 ፩. በጠቅላላ የሥራ ተቋራጭነት የኮንስትራክሽን ሥራዎችን በተናጠል ወይም በቅንጅት መሥራት፣
 ፪. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ማከራየት፣
 ፫. የእሸት እና የደረቅ ቡና መፈልፈያና ማጠቢያዎችን መገንባትና መጠገን፣
 ፬. የእሸትና ደረቅ ቡና መፈልፈያና ማጠቢያ እንዲሁም ሌሎ የእርሻ መሣሪያዎችን ማምረት፣ መገጣጠም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ከውጭ ሀገር እያስመጣ መሸጥ፣
 ፭. የእንጨት፣ የበረታ ብረት የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ማምረትና መሸጥ፣
 ፮. ዓላማዎቹን ■ግቡ ለማድረስ የሚረዳ ተዛማጅ ሥራዎንችን መሥራት፣

፮. <u>ካፒታል</u>
የድርጅቱ ካፒታል ብር 14,718,830.00/አሥራ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሠላሳ ብር/ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. <u>ኃላፊነት</u>
ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>
ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>
በደንብ ቁጥር ፩፻፶/ ፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበው የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያና ምሕንድስና ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፏል፡፡

፲. <u>የተሻረ ሕግ</u>
የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያና ምሕንድስና ድርጅትን ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶/፲፱፻፹፮ በዚህ ደንብ ተሸሯል፡፡

፲፩. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስተር

3. *Supervising Authority.*
A body to be designated by the Government shall be the Supervising Authority of the Enterprise.

4. *Head Office*
The Enterprise shall have its head office is Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Objectives*
 1. To engage in construction works as a General Contractor Unilaterally or in joint ventures;
 2. To lease Construction Machineries and Equipment;
 3. To engage in the Construction and Maintenance of Coffee Cherry Pulping and dry coffee hulling stations;
 4. To manufacture, Assemble and Import when necessary Coffee cherry pulping and dry coffee hulling machines and other agricultural implements and distribute same;
 5. To engage in the manufacturing and marketing of wooden and metallic Construction materials and to undertake agricultural implements maintenance services;
 6. To engage in other related activities necessary for the attainment of its objectives.

6. *Capital*
The capital of the Enterprise is Birr 14,718,830.00 (Fourteen Million Seven Hundred Eighteen Thousand Eight Hundred thirty birr) which is paid in cash and in kind.

7. *Liability*
The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. *Duration*
The Enterprise is established for and indefinite duration.

9. *Transfer of Rights and Obligations*
The rights and obligations of the Coffee Technology Development and Engineering Enterprise, which was established by regulation No. 150/1993, are hereby transferred to the Enterprise.

10. *Repeal*
Coffee Technology Development and Engineering Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 150/1993 is hereby Repealed.

11. Effective Date
These Regulations shall come into force as of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, This 22[nd] day July/2005

*MELES ZENAWI*
*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRRINTING ENTERPRISE